የወ/መ/ቁጥር 160099

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ 1 ኛ ስማዕኒ ይሁኔ ውቤ - ቀረበ

2 ኛ አፈወርቅ በላይ ጌታሁን - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ መስከረም 11 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የክስ አቤቱታ ተከሳሾች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ) እና 556(2)(ሀ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ሐምሌ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት ከሌሊቱ 11፡40 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ልዩ ቦታው አቡነ ሀብተማርያም ቤተክርስቲያን አካባቢ የግል ተበዳይ አባ ሀይለማርያምን አንደኛ ተከሳሽ በእንጨት ዱላ ወገባቸውን መትቶ ሲያሳምማቸው፤ ሁለተኛ ተከሳሽ የግራ እግራቸውን በዱላ መትቶ ያሳበጠ በመሆኑ በግብረአበርነት በፈፀሙት ቀላል የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሾች ደርሷቸውና ተነቦላቸው ከተረዱት በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ፤ ድርጊቱን አልፈፀምንም፤ ጥፋተኞችም አይደለንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሁለት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የተሰሙት ምስክሮችም በክሱ ላይ በተገለፀው ጊዜ፤ ቦታና ሰዓት ሁለቱም ተከሳሾች ጨለማን ተገን በማድረግ የግል ተበዳይና ሁለተኛው ምስክር ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ሲሄዱ እዚያው አቡነ ሀብተማርያም ቤት ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ዱላ ይዘው የግል ተበዳይን ጀርባና እግር በመምታት ጉዳት ያደረሱባቸው መሆኑን፤ በዕለቱም ጩኸት ተበዳይና ምስክሩ ሲያሰሙ ተከሳሾች ሮጠው ማምለጣቸውን፤ በወቅቱ የግል ተበዳይ አፈወርቅ የተባለውን ተከሳሽ በመያዝ ሲታገል እንደነበር በዝርዝር ያስረዱ ሲሆን፤ በግል ተበዳይ አካል ላይም ጉዳቱ የደረሰባቸው መሆኑን የህክምና ማስረጃ ቀርቧል፤ በዚህም መሰረት ዐ/ሕግ ክሱን በሰውና በሰነድ ማስረጃ ያረጋገጠ ስለሆነ ተከሳሾች በተከሰሱበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ስር እንዲከላከሉ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዘዋል።

ተከሳሾችም እንከላከላለን ብለው የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም ያስመዘገቡት፤ አንደኛ ተከሳሽ በዕለቱ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንዳለደርኩ፤ ያደርኩትም መካኒሳ ካለ ቤት ውስጥ ስለመሆኑ ቁስ ቸሬ በሱፈቃድ፤ መምህር ዮሐንስ ገላው እና መሪጌታ ብርሀን መኮንን ያስረዱልኛል ሲል፤ ሁለተኛ ተከሳሽ ደግሞ እኔ ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ከተከራየሁት ቤት ያደርኩና ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ሰዓትና ጊዜ ያለመኖሬን ቁስ ቸሬ በሱፈቃድ፤ አባ ወ/ገብርኤል ተጠምቀ መድህንና ወ/ሮ ታሪኳ የተባሉት የመከላከያ ምስክሮቹ ያስረዱልኛል በማለት አስመዝግበው የመከላከያ ምስክሮቹም እንደ እምነታቸው መጋላ ከፈፀሙ በኋላ የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል። ከዚህ ሌላ ፍ/ቤቱ በተጨማሪ ምስክርነት ስድስት ምስክሮችን በወቅቱ በቦታው ነበሩ ወይም በግል ተበዳይ ላይ የደረሰውን ጉዳት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ያውቃሉ የተባሉትን አስቀርቦ የሰማ ሲሆን፤ በዐ/ሕግ በኩልም ሁለት ተጨማሪ ምስክሮች እንዲሰሙለት ጠይቆ ከተፈቀደለት በኋላ ቀርበው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሾች በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ አስተባብለዋል ወይ የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት በመያዝ በተጨማሪነት ከተሰሙት ምስክሮች ቃል ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል። በዚህም መሰረት ሐምሌ 14 ቀን 2001 ዓ.ም ለሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም አጥቢያ የግል ተበዳይ አባ ኃ/ማርያም ገረመው በቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠና የተከሳሾች የመከላከያ ምስክሮችም ያረጋገጡት ጉዳይ ነው። ጉዳቱንም የአሁን ተከሳሾች ነው ያደረሱት በማለት ዐ/ሕግ ማስረጃ አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ተከሳሾች ደግሞ እኛ በወቅቱ በቦታው አልነበርንም፤ ያደርነውም ከቤተ ክርስቲያኑ ውጭ ሌላ ቦታ ነው በማለት ክርክርና ማስረጃ አስምተዋል። የአንደኛ ተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮች በሰጡት ምስክርነት ላይ አንደኛው ሦስት ሆነን ነው ቤት ውስጥ ያደርነው ሲል፤ ሌላኛው ደግሞ አራት ሆነን ነው ያደርነው በማለት ተናግሯል። ይህ ደግሞ በአንድ ተመሳሳይ ነጥብ ላይ እምነት ሊጣልበት የማይችል የተለያየ የምስክርነት ቃል ስለሆነ ፍ/ቤቱ ምስክሮቹ ተአማኒነት ስለሌላቸው የምስክርነት ቃላቸውም ተቀባይነት የለውም ብሏል። የሁለተኛው ተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮችን ቃልንም ስንመረምር ከክፍለ ሀገር መጣ የተባለው ምስክር በምን ምክንያት እንደመጣ ግልፅ ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ምስክርነቱ ተከሳሹን ነፃ ለማውጣት የቀረበ ነው ከሚል ውጭ እውነት ነው ብሎ ለመቀበል አልቻለም። ከዚህ ሌላ በወቅቱ ተከሳሾች ተረኛ የበቱ ክርስቲያኑ ሰሞነኛ አገልጋዮች እንደነበሩና እዚያው ቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ እንዳደሩ ተቆጣጣሪያቸው ጭምር ቀርበው የመሰከሩ ሲሆን፤ ከዚያ ዕለት በኋላ ተከሳሾች ጠፍተው ሰንብተው በፖሊስ የተያዙ መሆናቸውን ተጨማሪ ምስክሮቹ ያስረዱ በመሆኑ ተከሳሾች በወቅቱ በቤተ ክርስቲያኑ አልነበርንም፤ ስለሆነም ድርጊቱን አልፈፀምንም በማለት ያቀረቡትን ክርክር ፍ/ቤቱ ውድቅ አድርጎ

ሁለቱንም ተከሳሾች በተከሰሱበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ) እና 556(2)(ሀ) ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ተወስኗል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ የምናቀርበው የቅጣት ማቅለያ የለም፤ ነገር ግን ተከሳሾች ድርጊቱን የፈፀሙት በጋራና በሌሊት ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1) (ሐ) እና (መ) መሰረት ፍ/ቤቱ ቅጣቱን በማክበድ እንዲወስን በማለት አመለከቱ።

<u>አንደኛ ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 24 ዓመት ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ 8ኛ ክፍል ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ የምረዳቸው ወንድሞች ግን አሉኝ፤ የወር ገቢዬ ብር 450 ነው፤ ለቤት ኪራይ በወር ብር 150.00 እከፍላለሁ በማለት አመለከተ።

<u>ሁለተኛ ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 20 ዓመት ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ 8ኛ ክፍል ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ የወር ገቢዬ ብር 532.00 ነው፤ እህትና ወንድም እረዳለሁ በማለት አመለከተ።

ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሮ የሚከተለው የቅጣት ውሳኔ ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ሊያሳካ እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ኩበደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሾች ጥፋተኛ የተባሉበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ደረጃ የወጣለት ወንጀል በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና አባሪ 3 መሰረት የተመለከተው ደረጃ 2 ሲሆን ተጓዳኝ መነሻ እርከኑም 5 ነው። ስለሆነም የዚህ

እርከን መነሻ ፈቃደ ስልጥን/range/ ከስድስት ወር እስከ ዘጠኝ ወር ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ፍ/ቤቱ የወሰነው መነሻ ቅጣት ሰባት ወር ቀላል እስራት ነው።

በዚህም መሰረት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ቅጣት ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1) (ሐ) እና (መ) መሰረት የቅጣት ማክበጃ ያቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ የመነሻውን ቅጣት እርከኑን በሁለቱ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ወደ እርከን 7 ከፍ ተደርጓል።

ተከሳሽ በበኩላቸው የቅጣት ማቅለያ አስተያየት ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 ላይ በተመለከቱት መሰረት በማስረጃ የተደገፉ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አላቀረቡም፤ በመሆኑም ፍ/ቤቱ የቅጣቱን እርከን ዝቅ አላደረገውም።

ስለሆም በማክበጃ ምክንያቱ መሰረት ከፍ ባለው መሰረት የእርከን 7 ፍቅድ ስልጣን ከአንድ ዓመት እስከ አንድ ዓመት ከሦስት ወር እስራት ስለሆነ ፍ/ቤቱ ተከሳሾች ለፈፀሙት ጥፋት ያርማቸዋል፤ ወደፊትም ያስተምራቸዋል ብሎ ባለነበት በአንድ ዓመት ከአንድ ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. በተከሳሾች ላይ የተወሰነውን የእስራት ቅጣት ማ/ቤት እንዲያስፈፅም ታዟል።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. በዚህ መዝገብ የተሰጠ የዋስትና ግዴታ ካለ ቀሪ ሆኗል።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።